# የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የአሠራር ደንብ

## ክፍል አንድ

### 1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣

### 1.1 አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የአሠራር ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.2 ደንቡን ያወጣው አካል

ይህን ደንብ ያወጣው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋር ምክር ቤት ነው፡፡

### 1.3 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ መጋቢት 5 ቀን 2011 ዓ.ም የቃል ኪዳን ሰነድ በፈረሙት እና ወደፊት በሚፈርሙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 1.4 ዓላማ

ይህ ደንብ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቋቋሙት የጋራ ምክር ቤት የሚያስፈጽማቸውን ዓላማዎች፤ የሚያከናውናቸውን ተግባራት እና ኃላፊነት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን፤ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች በቃል ኪዳን ሰነዱ እና ተያያዥነት ባላቸው የምርጫ ሕግ ድንጋጌዎች የተጣለባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነ ት የሚያከናውኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

### 2. የምክር ቤቱ ስራ አመራር እና የስብሰባ ስነ ስርዓት

### 2.1 የምክር ቤቱ ስራ አመራር እና አሰራር

2.1.1 የጋራ ምክር ቤቱ ስራውን የሚያከናውነው በጠቅላላ ስብሰባ እና በልዩ ልዩ ኮሚቴዎች እራሱን በማደራጀት ነው፡፡

## 2.2 <u>የምክር ቤቱ ስብሰባ</u>

2.2.1 የጋራ ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በዓመት ውስጥ አራት ጊዜ ይሆናል፡፡ የስብሰባው የጊዜ ሰሌዳ በጀመሪያው የምክር ቤቱ ጉባኤ ይወሰናል፡፡ ይሁንና በምርጫ ወቅት የጋራ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ስብሰባ በየወሩ ይሆናል፡፡

2.2.2 የጋራ ምክር ቤቱን ከመደበኛው የስብሰባ ጊዜ ውጪ መጥራት የሚያስፈልግ ጉዳይ ሲያጋጥም የምክር ቤቱ 1/3 አባላት ወይም ሰብሰሳቢው፣ ምክትል ሰብሳቢው እና ዋና ፀሐፊው አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ይገባል ብለው ካመኑ ወይም የምርጫ ቦርድ ጥያቄው በቀረበ በ15 ቀን ውስጥ መጥራት ይችላሉ፡፡

2.2.3 የምክር ቤቱ ምልአተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው የምክር ቤቱ 50+1 አባላት በተጠራው ስብሰባ ላይ ሲገኙ ነው፡፡

2.2.4 የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ምልዐተ ጉባኤ ካልተሟላ ሌላ ስብሰባ በ15 ቀን ውስጥ እንዲጠራ ይደረጋል፡፡ ድጋሚ በተጠራው ስብሰባ በተገኙ አባላት ስብሰባው ይካሄዳል ውሳኔም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ካጋጠሙ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 2.3 <u>የምክር ቤቱ ሰብሳቢ</u>

2.3.1 የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፡፡ የስራ ዘመኑም 6 ወር ይሆናል፡፡ ይሁን እና አንዴ በድጋሜ መመረጥ ይችላል፡፡

2.3.2 ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን ከም/ሰብሳቢው እና ከጸሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ ለአባላት ከስብሰባ በፊት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

2.3.3 የምክር ቤቱን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡

## 2.4 <u>የምክር ቤቱ ም/ሰብሳቢ</u>

2.4.1 የምክር ቤቱ ም/ሰብሳቢ በጋራ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፡፡ የስራ ዘመኑም 6 ወር ይሆናል፡፡ ይሁን እና አንዴ በድጋሜ መመረጥ ይችላል፡፡

2.4.2 ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ም/ሰብሳቢው ስብሰባዎቹን ይመራል፡፡

2.4.3 ሌሎች በሰብሳቢው ተለይቶ የሚሰጠውን ስራዎች ይሰራል፡፡

## 2.5 ዋና ጸሐፊ

2.5.1 የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ በጋራ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፡፡ የስራ ዘመኑም 6 ወር ይሆናል፡፡ ይሁን እና አንዴ በድጋሚ መመረጥ ይችላል፡፡

2.5.2 በምክር ቤቱ አባላት ላይ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች፣ መልሶች ከሰብሳቢው ጋር በመምከር ለሚመለከተው ኮሚቴ ይመራል፡፡

2.5.3 በአቤቱታዎቹ ላይ ከአጣሪ ኮሚቴ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ከሰብሳቢው ጋር በመምከር ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

2.5.4 የጋራ ምክር ቤቱን ውሳኔም ከሰብሳቢው፣ ከም/ሰብሳቢው ጋር ሆኖ ያስፈጽማል፡፡

2.5.5 የምክር ቤቱን ቃለ ጉባኤዎች፣ በመዝገብ ይይዛል፡፡ እንዲሁም የአጣሪ ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳቦችን፣ የአስማሚ ሰነዶችን እና የጋራ ምክር ቤቱ ውሳኔዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ፓርቲዎች መዝገብ ጋር እንዲያያዝ ያደርጋል፡፡

2.5.6 በምክር ቤቱ በሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ውስጥ በጸሐፊነት ከሚመደቡ አባላት ጋር በጋራ በመስራት የኮሚቴዎች ቃለ ጉባኤዎች በደንብ መፃፋቸውንና በመዝገብ መያዛቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 2.6 የስብሰባ ስነ ስርዓት

2.6.1 ከጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

2.6.2 የጉባኤው አባላት ውሳኔዎችን በስምምነት ያሳልፋል፤ ሆኖም የስምምነት ውሳኔ ማስተላለፍ ካልተቻለ በጉባኤው ውስጥ በተገኙ አባላት ¾ ድምጽ ውሳኔዎቹ ይተላለፋሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## 3. ስለ<u>ኮሚቴዎች</u>

### 3.1 <u>የኮሚቴዎች አወቃቀር</u>

3.1.1 ምክር ቤቱ ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንዲችል ከ አምስት እስከ ሰባት የሆኑ የምክር ቤቱን አባላትን የያዘ ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ተግባርና ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

3.1.2 ከዚህ በላይ በተገለጸው መሰረት ምክር ቤቱ የሚከተሉትን ኮሚቴዎች ያደራጃል፡፡

ሀ) በጀት ኮሚቴ፤

ለ) የቁጥጥር እና የኦዲት ኮሚቴ፤

ሐ) የሚዲያ አጠቃቀም ኮሚቴ፤

መ) የአቅም ግንባታ ኮሚቴ፤

ሠ) አጣሪ ኮሚቴ፤

ረ) የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ፤

3.1.3 የኮሚቴው አባላት የተመደቡበትን ኃላፊነት በማናቸውም ምክንያት ለሌላ የምክር ቤቱ አባል ወይም ለሌላ ወገን ውክልና በመስጠት ሊያሰሩ አይችሉም፡፡

3.1.4 ኮሚቴዎቹ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ስራቸውን ይሰራሉ፡፡

### 3.2 <u>የስብሰባ ስነ ሥርዓት</u>

3.2.1 እያንዳንዱ ኮሚቴ የመሰብሰቢያውን ቦታ እና ጊዜ ይወስናል፡፡

3.2.2 የኮሚቴው አባላት 50+1 ከተገኙ ምልዐት ጉባኤው ተሟልቷል፡፡

3.2.3 ኮሚቴዎችም የራሳቸውን ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ይመርጣሉ፡፡

3.2.4 ሰብሳቢው ከኮሚቴው ዋና ጸሐፊ ጋር በመሆን የኮሚቴውን አጀንዳ ይቀርፃል፣ ስብሰባዎችንም ይመራል፡፡

3.2.5 የኮሚቴው ም/ሰብሳቢ ሰብሳቢው በሌለበት ጊዜ ሁሉ ሰብሳቢውን ተክቶ ስብሰባዎችን ይመራል፡፡ በሰብሳቢው የተሰጠውን ሌላ ተጨማሪ ስራ ይሰራል፡፡

3.2.6 የኮሚቴው ጸሐፊ የኮሚቴዎቹን ቃለ ጉባኤዎች በአግባቡ ይይዛሉ፡፡ ከጋራ ምክር ቤቱ ጸሐፊ ጋር በመሆንም ሰነዶቹ በደንብ የሚቀመጡበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡

## 3.3 <u>አባላት የሥራ ዘመን እና ግዴታ</u>

3.3.1 የኮሚቴዎቹ አባላት በጋራ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል፡፡

3.3.2 በምክር ቤቱ የሚመረጡ የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት የሥራ ዘመን አንድ ዓመት ይሆናል፡

ምክር ቤቱ ካመነ የሥራ ዘመኑ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ ለማራዘም ይችላል፡፡

3.3.3 ማንኛውም የኮሚቴ አባል የተመደበበትን ሥራ በኃላፊነት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

3.3.4 የጋራ ምክር ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ኮሚቴዎችን ማቋቋም ይችላል፡፡

3.3.5 አንድ ፓርቲ ከአንድ ኮሚቴ በላይ ተሳታፊ ሊሆን አይችልም፡፡

## 3.4 <u>አባላት ሥራቸውን የሚለቁበት ሁኔታ</u>

3.4.1 አንድ የኮሚቴ አባል የተመደበበት የሥራ ኃላፊነት እየተወጣ አለመሆኑ በምክር ቤቱ ሲታመን ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ምክር ቤቱ ይወስናል፡፡

3.4.2 አንድ የኮሚቴ አባል ከደንብ መተላለፍ ውጪ በወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት ወዲያውኑ ከተመደበበት ሥራ ላይ እንዲነሳ ምክር ቤቱ ይወስናል፡፡

3.4.3 አንድ የኮሚቴ አባል የተመደበበትን ሥራ በጤና ችግር ምክንያት ማከናወን አልቻለም ተብሎ ሲታመን እና ምክር ቤቱ ሲወስን ከተመደበበት ኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ ይሁንና ፓርቲው ተለዋጭ አባል በጽሑፍ የመመደብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

3.4.4 አንድ የኮሚቴ አባል የቃል ኪዳኑ ሰነድ እንዲሁም ምክር ቤቱ ያወጣቸውን ደንቦች ያለማክበሩ በምክር ቤቱ ሲረጋገጥ ከኮሚቴው አባልነት እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

4. <u>የኮሚቴዎች ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

4.1 <u>የበጀት እና ፋይናንስ ኮሚቴ</u>

4.1.1 የጋራ ምክር ቤቱ ያቋቋመው ድርጅት እና የፋይናንስ ኮሚቴ የጋራ ምክር ቤቱ ስራውን የሚሰራበት ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤ ለምክር ቤቱም አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

4.1.2 ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 4.1 የፀደቀውን በጀት በተመለከተ ኮሚቴው ለምርጫ ቦርድ አቅርቦ ያስፈፅማል፡፡

4.1.3 ቦርዱም በፀደቀው በጀት መሰረት ለጋራ ምክር ቤቱ የሰጠው ገንዘብ በአግባቡ ለታሰበለት ጉዳይ መዋሉን ይቆጣጠራል፡፡ ለታሰበለት ጉዳይም አልዋለም ብሎ ባመነ በማናቸውም ጊዜ ጉዳዩን ለጋራ ምክር ቤቱ አቅርቦ እንዲጣራ ያስደርጋል፡፡ በማጣራቱ ሂደት የተገኘውንም ውጤት ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

4.2 <u>የቁጥጥር እና የኦዲት ኮሚቴ</u>

4.2.1 የቁጥጥር እና የኦዲት ኮሚቴ የጋራ ምክር ቤቱን ዓመታዊ የስራ ክንውን እንዲሁም የፋይናንስ አፈፃፀሙን የመመርመር ኃላፊነት አለበት፡፡

4.2.2 ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 4.2.1 በተገለፀው መሰረት የተገኘውን የምርመራ ውጤት ለጋራ ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

4.3 <u>የሚዲያ አጠቃቀም ኮሚቴ</u>

4.3.1 በጋራ ምክር ቤቱ አባላት የመንግሥትም ሆነ የግል ሚዲያ ሲጠቀሙ ዲሞክራሲያዊ ባህልን ለማሳደግ በሚቻልበት መልክ የሚፈልጉትን መልዕክት ማስተላለፍ ወይም አለማስተላለፋቸውን፤ መልዕክቶቻቸው ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ተገቢውን ሚና መጫወት አለመጫወታቸውን ይመረምራል፡፡

4.3.2 የጋራ ምክር ቤቱ አባለት የሚዲያ ተቋማት አሰራሮች ነፃነት የሚጋፉ ስራዎችን እንዳይሰሩ ይቆጣጠራል፡፡ ሰርተውም ከተገኙ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

4.3.3 የጋር ምክር ቤቱ አባላት በደጋፊዎቻቸው፣ በአባሎቻቸውም ወይም በራሳቸው ባለቤትነት በተያዙ ሚዲያዎች የሚተላለፉ ማናቸውም ጥላቻን፣ መቃቃርን፣ አመፃን፣ መለያየትን እና ሕገወጥ ድርጊቶች የሚያደፋፍሩ መልዕክቶች እንዳይወጡ ይመክራል፣ ይቆጣጠራል ሆኖም ከተገኘ ለጋራ ምክር ቤቱ ሪፖርት በማቅረብ ተገቢውን እርምጃ ያስወስዳል፡፡

## 4.4 <u>የአቅም ግንባታ ኮሚቴ</u>

4.4.1 የጋራ ምክር ቤቱ የሚያቋቁመው የአቅም ግንባታ ኮሚቴ የቃል ኪዳኑ ፈራሚ ፓርቲዎች ለአባሎቻቸው እና ለደጋፊዎቻቸው በቃል ኪዳን ሰነዱ መሠረት ትምሕርት መስጠታቸውን ይከታተላል፡፡

4.4.2 የጋራ ምክር ቤቱ አባላት የሆኑ ፓርቲዎች የሌላውን ፓርቲ አባላት ደጋፊ እንዲሁም በየትኛውም አካባቢ የሚገኝ የማኅበረሰብ ክፍልን መብትና ነፃነት ማክበር ያለባቸው ስለመሆኑ ትምህርት መስጠታቸውን እና በተግባር ማዋላቸውን ይከታተላል፡፡

4.4.3 በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በሀይማኖት ወይም በሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ መሰረት ያደረጉ ጥፋቶች በደጋፊዎቻቸው፣ በአባሎቻቸው እንዳይፈፀም የማስተማር ግዴታቸውን ስለመወጣታቸው በቅርብ ይከታተላል፡፡

4.4.4 የጋራ ምክር ቤቱ አባላት በሚዲያ እና በማህበራዊ ገፆች የሚያወጧቸው መረጃዎች፣ ቅስቀሳዎች ከሰነዱ ጋር የማይፃረሩ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

4.4.5 ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለፀውን ሁኔታ የተፃረረ የጋራ ምክር ቤት አባል ሲገኝ ለምክር ቤቱ ሪፖርት በማቅረብ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## 4.5 <u>አጣሪ ኮሚቴ</u>

4.5.1 የቃል ኪዳኑ ሰነድ ተጥሷል ብሎ የሚያምን ወገን በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ አቤቱታውን ሲያቀርብ፤ ይህንኑ አቤቱታ ብቻ የሚመረምር እና የውሳኔ ሀሳብ ለጋራ ምክር ቤቱ

የሚያቀርብ ጊዜአዊ ኮሚቴ ነው፡፡ የኮሚቴው ዝርዝር የሥራ አፈፃፀም የቃል ኪዳን ሰነዱን ለማስፈፀም በወጣው የስነ ሥርዓት ደንብ ውስጥ ይደነገጋል፡፡

### 4.6 <u>የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ</u>

የጋራ ምክር ቤቱን አላማ፣ ተግባርና ኃላፊነት የሚያስፈፅም የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ ይኖራል፡፡ ዝርዝር ሥራውን የጋራ ምክር ቤቱ ያወጣል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

### 5. <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 5.1 <u>ማሻሻያ</u>

የጋራ ምክር ቤቱ ይህን የውስጥ የአሰራር ደንብ ማሻሻል ያስፈልጋል ብሎ በአመነ በማናቸውም ጊዜ የማሻሻል ስልጣን አለው፡፡ ደንቡም የሚሻሻለው በአባላት ሙሉ ስምምነት ነው፡፡ ይሁን እና ሙሉ ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ በምክር ቤቱ አባላት ¾ተኛ ድምጽ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 5.2 <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የጋራ ምክር ቤቱ አባላት በፊርማቸው ከአጸደቁበት ከዛሬ ሚያዝያ 5 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት | | |
| 2 | የኢትዮጵያ ሰላማዊ የዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 3 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 4 | የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 5 | የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት | | |
| 6 | ገዳ ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ | | |
| 7 | የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 8 | መላው ኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 9 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ | | |
| 10 | የመላው ኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 11 | ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 12 | የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ | | |
| 13 | የወለኔ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 14 | የመላው ኦሮሞ ህዝብ ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 15 | የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ | | |
| 16 | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ | | |
| 17 | ሰማያዊ ፓርቲ | | |
| 18 | የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ | | |
| 19 | አዲስ ትውልድ ፓርቲ | | |
| 20 | የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |
| 21 | አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ | | |
| 22 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ኮንግረስ | | |
| 23 | ምክክር ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 24 | የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ | | |
| 25 | ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ | | |
| 26 | የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 27 | ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 28 | የምዕራብ ሶማሌ ዲሞክራቲክ ፓርቲ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 29 | የሐረሪ ብሔራዊ ሊግ | | |
| 30 | የኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር | | |
| 31 | የደንጣ፣ ዱባሞ ክችንችላ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 32 | የከምባታ ሕዝቦች ኮንግረስ | | |
| 33 | የትግሪ ወርጂ ብሔረሰብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 34 | የኦሮሞ ነጻነት አንድነት ግንባር | | |
| 35 | የዶንጋ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 36 | የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ | | |
| 37 | የኢትዮጵያዊያን አንድነት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 38 | የኢትዮጵያ ሶማሌ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 39 | የሐድያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 40 | የጌዴኦ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 41 | የየም ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 42 | የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 43 | የኦሮሚያ ነጻነት ብሔራዊ ፓርቲ | | |
| 44 | የኦሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት | | |
| 45 | የሲዳማ አርነት ንቅናቄ | | |
| 46 | የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 47 | የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 48 | ዱቤና ደገኒ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | ፓርቲ | | |
| 49 | የዲል ወቢ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 50 | የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር | | |
| 51 | የሲዳማ ሀዲቾ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 52 | የቤንች ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 53 | የሸኮና አካባቢው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 54 | ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲ ሉዓላዊነት | | |
| 55 | የአርጎባ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 56 | የሐረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት | | |
| 57 | የጋምቤላ ሕዝቦች አንድነት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 58 | የአርጐባ ብሔረሰብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 59 | የቤንሻንጉልና ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 60 | የአገው ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 61 | የጉምዝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 62 | የቤንሻንጉል ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ ለሠላምና ለዴሞክራሲ ድርጅት | | |
| 63 | የስልጤ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 64 | የደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኮንግረስ | | |
| 65 | የጋምቤላ ህዝቦች ነፃነት ንቅናቄ | | |
| 66 | የቅማንት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 67 | ኢትዮጵያዊያን ሀገር አቀፍ ንቅናቄ | | |
| 68 | የኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ | | |
| 69 | የኦሮሚያ ብሔራዊ ፓርቲ | | |
| 70 | የአገው ብሔራዊ ሸንጎ | | |
| 71 | ነፃነት ለአንድነትና ለፍትሕ ፓርቲ | | |
| 72 | የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ | | |
| 73 | ነፃነትና ሰላም ለኢትዮጵያ ኅብረት ፓርቲ /ሰላም/ | | |
| 74 | የአፋር ሕዝብ ፓርቲ | | |
| 75 | የጋምቤላ ሕዝቦች ፍትህ ለሰላምና ልማት ዲሞክራቲክ ንቅናቄ /ጋህፍሠልዲን/ | | |
| 76 | የአፋር ሕዝብ ነፃነት ፓርቲ /አህነፓ/ | | |
| 77 | ነፀብራቀ አማራ ድርጅት /ነአድ/ | | |
| 78 | የአፋር ሕዝቦች ፍትሐዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 79 | የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር ፓርቲ | | |
| 80 | የቁጫ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 81 | ሞቻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ | | |
| 82 | የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ህብረት /ደምኢህ-ህብረት/ | | |
| 83 | የጋምቤላ ክልላዊ ንቅናቄ | | |
| 84 | የሲዳማ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /ሲብዴፓ/ | | |
| 85 | አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 86 | የኢትዮጵያ አረንጓዴ ሊብራል ፓርቲ | | |
| 87 | የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ | | |
| 88 | የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ንቅናቄ /ኢብን/ | | |
| 89 | የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር /ትዴት/ | | |
| 90 | የአማራ ሕልውና ለኢትዮጵያ አንድነት | | |
| 91 | ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ /ኢትዮጵያችን/ | | |
| 92 | የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር | | |
| 93 | የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኦዴግ/ | | |
| 94 | የኦሮሚያ ነፃነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር | | |
| 95 | የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር /ኦብነግ/ | | |
| 96 | ሐረሪ ሪቫይቫል ንቅናቄ | | |
| 97 | የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ | | |
| 98 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሽግግር ም/ቤት /ሽግግር/ | | |
| 99 | የኢትዮጵያ ነፃነት ፓርቲ | | |
| 100 | የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ /መድህን/ | | |
| 101 | ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ | | |
| 102 | የኢትዮጵያ ኅብረሕዝብ ብሔራዊ ንቅናቄ /ኅብረሕዝብ/ | | |
| 103 | የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ | | |
| 104 | ቱሳ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት /ቱሳ/ | | |
| 105 | ደቡብ አረንጓዴ ኮከብ ኅብረት | | |

| ተ.ቁ. | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 106 | የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ኅብረት | | |
| 107 | የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት ፓርቲ /ኢሕዴኅፓ/ | | |
| 108 | ብሩህ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ብሩህ/ | | |
| 109 | የኦሮሞ አንድነትና ዴሞክራሲ የፌዴራል የሠላም ለውጥ ፓርቲ | | |
| 110 | የተባበሩት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር | | |
| 111 | የጉራጌ ሕዝባዊ ንቅናቄ | | |
| 112 | አንድነት ለሰላምና ለእኩልነት ዲሞክራሲ ፓርቲ | | |
| 113 | የአዲስ አበባ ሕዝብ ፓርቲ | | |
| 114 | ብሔራዊ ተሀድሶ ለሰላም ልማት | | |
| 115 | የኢትዮጵያ ሪፐብሊካን ፓርቲ | | |
| 116 | የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |